# ግንቦት 7
# በድል ወይስ በገደል አፋፍ!!

ግንቦት 7 ያለፈው 2004 አመትን እንደምን አሳለፈው? አዲሱን የ2005 አመትንስ እንደምን ተቀበለው? በዚህ ጉዳይ የግንቦት 7 አምባገነን መሪዎች ትንተና እና የአብዛኛው አባል መሬት ላይ ያለ ተጨባጭ ሁኔታ ግምገማ ለየቅል እንደሆነ ምንም ጥያቄ የለውም::

መሪዎቻችን ግንቦት 7 ለያዥ ለገራዥ እስኪያስቸግር ድረስ በየእለቱ በድል ጎዳና እየገሰገሰ ነው፣ እንዲያውም እባካችሁ ጊዜ የለንም ፍጠኑ እያሉ ምንም ነገር በሌለበት ሁኔታ "ለድል" እነሱ የተጣዳፉ መስለው እኛን ሊያጣድፉ ይውተረተራሉ:: አባሉ በበኩሉ እናንተ የምትሉት ሁሉ ውሸት ነው፣ ድርጅቱ አራት አመት ሙሉ ምንም ነገር ሳይሰራ እንደውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ በመሄዱ በርካታ አባላት በሁኔታችሁና በአመራራችሁ ተስፋ እየቆረጡ በራሳቸው ፈቃድ ድርጅቱን እየለቀቁ በመውጣት ላይ ናቸው፣ አሁን ያሉትም ቢሆን የአባልነት ግዴታቸውን በአግባቡ እየተወጡ አይደለም ከዚህም አልፎ በድርጅታችን ውስጣዊ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ህይወት ጠፍቷል፣ መሪዎቻችን የአባሉን ቅሬታ ማዳመጥ የተሳናቸው የለየላቸው አምባገነኖች ሆነዋል ይላል:: ጉደኛ መሪዎቻችን በበኩላቸው የለም እንደዚህ አይነት ጥያቄ የሚያነሱ በተለይ ምንም አልሰራችሁም የሚሉን አባላት ድርጅቱ መሬት ላይ ምን እየሰራ እንደሆነ ስለማያውቁ ነው፣ የክረምቱ ዝናብና የወንዞች ሙላት አላንቀሳቀስ ብሎን ነው እንጂ መሬቱ ትንሽ ጠፈፍ ማለት ሲጀምር ግድ የለም! በኛ ይሁንባችሁ "ተአምር" ታያላችሁ ይሉናል:: በግንቦት 7 ውስጥ ዴሞክራሲ የለም፣ የድርጅቱ ህገ-ደንብ አይከበረም፣ አምባገነንነት ሰፍኗል ስለሚሉት አባላት ሲጠየቁ ደግሞ አይ እነሱ'ማ ባለጌዎችና ነውረኞች ናቸው እንደውም እኛኑም ጭምር የሚያቆሽሹ ጭቃዎች ስለሆኑ ሌላውን ሳያበላሹ በአስቸኳይ ከድርጅቱ መወገድ አለባቸው ይላሉ:: እንግዲህ 2004ን ምንም ቁምነገር ሳንሰራ አመቱን ሙሉ በዚህ አይነት ጭቅጭቅ እና ንትርክ ጊዜያችንን እንዳሳለፍን ሁሉም የግንቦት 7 አባል የሚያውቀው እውነት ነው::

ወጉ እንዳይቀር የድርጅቱ ሊቀመንበር አስካዱ (ብርሃኑ ነጋ) ለአዲስ አመት የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ያስተላልፋል ሲባል አዲስ ነገር እንደማይናገር ብናውቅም ንግግሩን ለማዳመጥ ሰፍ ብሎ የጠበቀ የግንቦት 7 አባል ብዙ ነው:: እንደገመትነውም በዚሁ የአዲስ አመት የእንኳን አደረሳችሁ መልእክቱ "ድርጅታችን ካከናወናቸው ተግባራት ውስጥ በሕዝብ ቢታወቁ ከጉዳታቸው ጥቅማቸው ያመዝናል የምላቸውን አነሳለሁ" በሚል በተለመደው የአራዳ ጮሌ የንግግሩ ስልቱ ዲስኩሩን የጀመረው አስካዱ በዚህ ዙርያ ተሰራ ስለሚባለው አንድም የረባ ቁም ነገር ማንሳት አልቻለም:: ከየት ይምጣ? የአቅም ግንባታ፣ ሃገራዊ ህብረት፣ የሚድያ ስራዎች በሚል ያነሳቸው ትልልቅ አርእስቶች ይዘታቸው ሲታይ ፍሬ የሌላቸው ገለባ የቃላት ክምር ናቸው:: መጨረሻ ላይም ሲጨንቀው ባለፈው አመት በራሳቸው ጊዜ ከቁጥጥራችን ውጪ በሆነ መንገድ በሃገራችን የተከሰቱትን የመምህራን አመፅ፣ የሙስሊም ኢትዮጵያውያን ተቃውሞ፣ የመነኩሳት ተቃውሞ በዋልድባ፣ የፓትሪያርኩና የመለስ ዜናዊ ህልፈት መልካም እድሎች እንደነበሩ በማተት በአዲሱ አመትም እነዚህና ሌሎች ተመሳሳይ እድሎች ሲፈጠሩ በሚገባ ተጠቅመን ወያኔን "ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ" ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመሆን "ፆም ፀሎት" እንድንይዝ የሚጠይቅ አይነት ይዘት ያለው መልእክት አስተላልፎልን ንግግሩን ቋጨ:: ይህንን ለመናገር አደበባይ ሲወጣ አለማፈሩ ይገርማል!!

የአስካዱ ተላላኪ ከመሆን የዘለለ ሚና የሌላቸው በተለይ የበታችነት ስሜት (inferiority complex) ኩፉኛ የሚያጠቃው አስተሳሰበ-ድሃው ካሌብ (አበበ ቦጋለ) እና እቃው ሚያዝያ (ታደሰ ብሩ) ደግሞ ከሰሞኑ በኢሳት የቴሌቭዥን መስኮት ብቅ ብለው ግንቦት 7 በድል አፋፍ ላይ ነው እያሉ ስለየትኛው ድርጅት እንደሚያወሩ ግራ ገብቶን እስከምንጠራጠር ድረስ ሲዋሹን ሰነበቱ፡፡ እነዚህ ለምልክት ያህል የተቀመጡ አፍ ያላቸው አሻንጉሊቶች ወያኔን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ ግንቦት 7 በአሁኑ ወቅት ተፈላጊ የሆነ ድርጅታዊ ብቃት፣ ሚድያ፣ ህብረትና ጉልበት ያለው ድርጅት ለመሆን በቅቷል በማለት አደባባይ ወጥተው በድፍረት የባጡን የቆጡን ሁሉ ሲቀባጥሩ የተከታተላቸው ሰው ሁሉ ገርሞታል፡፡ ዳሩ ምን ህሊና ፈጠረባቸውና ያፍራሉ፡፡ የድርጅቱን ጉድ የሚያውቀው የግንቦት 7 አባል ግን በእነሱ ውሸት በጣም ተናደደ ወቸው ጉድ! እያለም በሃፍረት ተሸማቀቀ፡፡

አብዛኛው አባላችን የሚጋራው የኛ ግምገማ ድርጅታችን ግንቦት 7 በደካማ አመራር እና በአምባገነኖቹ መሪዎቻችን ግትር አቋም ምክንያት በ2004 አመት ምህረት ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ የተዳከመበት አመት ነው፡፡ አምባገነኖቹ መሪዎች ድርጅቱን ይዘው ለመውደቅ በተያያዙት የቁልቁለት መንገድ እንዲጓዙ እስከፈቀድንላቸው ድረስ ደግሞ ግንቦት 7 በአዲሱ አመትም ቢሆን ሌላው ቀርቶ በህይወት ለመሰንበትም እጅግ አዳጋች እንደሚሆንበት በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን፡፡ ለዚሁም የድርጅታችንን ትክክለኛ ወቅታዊ ስዕል የሚያሳዩ የሚከተሉትን ጭብጦችና ጠቋሚ ሃሳቦችን በአስረጅነት ለማስቀመጥ እንሻለን፡፡

1. የድርጅቱ አምባገነን መሪዎች በአባላት የተነሱ የመብትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን በሰለጠነ መንገድ በውይይት ለመፍታት ጥረት ከማድረግ ይልቅ ጥያቄ ያነሱ አባላትን የማባረርና የማገድ እርምጃዎች መውሰድን በመምረጣቸው ድርጅታችን ግንቦት 7ን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ እነዚህ ከድርጅቱ እንዲባረሩ የተወሰነባቸው እና በድርጅቱ በተለያየ የሃላፊነት ቦታ ላይ የነበሩት አባላት ከድርጅቱ ተገንጥለው በመውጣት "ግንቦት 7 ዲሞክራቲክ" የሚባል ድርጅት የማቋቋም እርምጃን ወስደዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ሁኔታው ወዴት ሊያመራ እንደሚችል በእርግጠኝነት መናገር የሚችል ሰው የለም፡፡ በእርምት ንቅናቄ ቡድኑና በእነዚህ አባላት ሲነሱ የቆዩ የዴሞክራሲ እና የድርጅቱ ህገ-ደንብ መከበር ጥያቄዎች የአብዛኛው አባል መሆናቸውን የሚያሳይ በቡድንም በተናጠልም ለአመራሩ ብዛት ያላቸው የቅሬታ ደብዳቤዎች እየጎረፉ መሆኑን እናውቃለን፡፡ ከእነዚህ መካከል በአፍሪካ አህጉር ከሚገኝ አንድ አባል በግንቦት 7 ውስጥ ስለሚታዩ ችግሮች በዝርዝር ፅፎ ለቱፋ (አንዳርጋቸው ፅጌ) በግል የላከው ደብዳቤ በወያኔነት ሲወነጅልዋቸው በከረሙት በእርምት ንቅናቄ ወይም በዴሞክራሲ ቡድኖች ሳይሆን በራሳቸው ለወያኔ ሚድያ እንዲደርስ አድርገውት እኛም አነበብነው፡፡ አምባገነን መሪዎቻችን ጥያቄ የሚያነሱ አባላትን ለማስወገድ በሸረቡት ሴራ ምክንያት የድርጅቱን መዋቅር በማፍረሳቸውና ይህንን ተከትሎ በድርጅቱ ውስጥ የተፈጠረውን የዴሞክራሲና የመብት ጥያቄ ለመፍታት ባለመቻላቸው ምክንያት በአሁኑ ወቅት ከላይ እስከታች ያለው የግንቦት 7 መዋቅር ከስራ ውጪ ሆኗል፡፡ ሌላ ቀርቶ ድርጅቱ ከአባላት በየወሩ ሲሰበሰብ የነበረው ወርሃዊ መዋጮ እንኳን በቅጡ መሰብሰብ በማይችልበት ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ የድርጅቱ አመራር ከላይ ተንሳፍፎ መሬት ላይ በሌለ ስራ አባላትን በማታለልና በማጭበርበር ተግባር ላይ ተጠምዷል፡፡ እነዚህ እና ሌሎች መሰል ውስጣዊ ችግሮቻችን የድርጅቱን ጥንካሬ አያመለክቱም፡፡ አመራሩ የመብት ጥያቄ ባነሱ አባላት ላይ ጣቱን ከመቀሰር ድክመቱን ተቀብሎ ራሱን ከስልጣን ማግለል፣ ግልፅና ዴሞክራሲያዊ የሆነ ውይይት እንዲካሄድ መፍቀድና ድርጅቱ ራሱን ለማጥራት የሚችልበት እድል እንዲመቻች ሁሉም አባል በያለበት በድፍረት አሁኑኑ መጠየቅ ካልጀመረ ድርጅቱን ከውድቀት ፈፅሞ ማዳን እንደማይቻል ሊረዳ ይገባል፡፡

2. ከወያኔ ጋር ለአባላት እኩል ሲደርስ የነበረው “እኔ ግንቦት 7” ወርሃዊ የውስጥ ጋዜጣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአባላትና ለትግሉ የሚጠቅም ፍሬ ያለው መረጃ ሳይዝ የዶክተር ተብዬው እቃ (ሚያዝያ) መጫወቻ ሆኖ ከከረመ በኋላ ህትመቱና ስርጭቱ ከቆመ እነሆ ሁለት ወራት አለፈው፡፡ አምባገነን መሪዎቻችን የጋዜጣው ህትመትና ስርጭት የተቋረጠው የአባላት ኢ-ሜይል ከመቀየር ጋር ተያይዞ በነበረው ሁኔታ ነው፣ አሁን ደግሞ የቴክኖሎጂ ግንኙነት ባለሙያዎች ጥናታቸውን ስላልጨረሱ ነው በማለት ሊያጭበረብሩን ይሞክራሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ግን ተራ የቅጥፈት ምክንያቶች ናቸው፡፡ እነሱ እንደሚሉት የግንቦት 7 አባላት ከሌላ ምንጭ ሊያገኙት የማይችሉ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግና ደህንነትን በመጠበቅ መካከል ሚዛን ለመጠበቅ ስለተጨነቁም አይደለም፡፡ የጋዜጣው ስርጭት ሊቋረጥ የቻለው የግንቦት 7 አባል ስለ ትግሉ ሂደት ከአመራሩ የሚጠብቀው እውነተኛና ጠቃሚ መረጃ ለማሰራጨት ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ስለደረሱ ብቻ ነው፡፡ የጋዜጣው ስርጭት የተቋረጠው እቃው ሚያዝያ በተለያየ የህይወት አጋጣሚ ያነበብናቸውና ማንበብ የምንችላቸውን የማኔጅመንት መፃህፍት ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ እየተረጎመ “ለግንቦት 7 አባላት አይን ብቻ” የሚል ምልክት እየለጠፈ ሲቀልድብን መክረሙ እነሱ ራሳቸውም እያሳፈራቸው ስለመጣ ብቻ ነው፡፡ ሌላ ምንም ምክንያት የላቸውም፡፡ ኢሳት በየእለቱ በሚያስተላልፋቸው “በሬ-ወለደ” አይነት የሃሰት ወሬዎች ምክንያት ሚድያውም ግንቦት 7ም እንደ ባለቤት በህዝብ አይን አመኔታን እያጡ እንዲመጡ እያደረገ መሆኑን ልብ ልንለው ይገባል፡፡ እንዲህ አይነት ሚድያዎች ይዘን ነው ግንቦት 7 ጠንካራ የሚድያ አቅም ገንብቷል እየተባለ የሚነገረን፡፡ በአጠቃላይ በሚድያ አቅማችን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ በድምር ሲታይ ድክመትን እንጂ ጥንካሬን የሚያመለክት አይደለም፡፡ አባላችን ብቻ ሳይሆን ደጋፊያችንና ህዝባችን ስለትግሉ ሂደት ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ የሚያገኙበት መንገድ እስካልተፈጠረ ድረስ በአጉል ተስፋ፣ በቅጥፈትና በሃሰት ወሬ ከአሁን በኋላ ረጅም ርቀት መጓዝ እንደማንችል አባሉ አውቆ እነዚህን አምባገነኖች ሊታገላቸው ይገባል፡፡

3. በአምባገነን መሪዎቻችን በጥምረት ስም ሲደለቅ የከረመው ዳንኪራም የትም አልደረሰም፡፡ በፀረ-ወያኔ ትግሉ ትርጉም ከሌላቸው ስብስቦች ጋር ውህደት ፈጥረናል እያሉ አባሉን ለማጭበርበር በከንቱ ቢደክሙም እስከአሁን ድረስ መሬት ላይ ጠብ የሚል ነገር አይታይም፡፡ ከከማል ገልቹ የኦነግ አንጃ ጋር ተፈጥሯል የተባለው ትብብር ፋይዳ የሌለው ነው፡፡ ጄኔራሉ በሻዕቢያ መሪዎች ትእዛዝ ከአስመራ መንቀሳቀስ የማይችል የቁም እስረኛ ሲሆን በስሩ የሚታዘዝ አንድም ወታደር የለውም፡፡ በአጠቃላይ ብዙ ሲነገርለት የከረመው ጥምረት የብርሃኑ ነጋ እና የነአምን ዘለቀ ጓደኝነት ሆኖ ቀርቷል፡፡ ምን አይነት አቅም ካለው እና ምን ከሚባል ድርጅት “እንደተዋሀድን” እንኳን በወጉ ሳይነገረን ሽር ጉዱ እንደቀጠለ ነው፡፡ ግንቦት 7ን የተቀላቀልነው በሌሎች ድርጅቶች ተንጠላጥለን ወይም በአጋጣሚ በሚፈጠሩ ማዕበሎች ተጠቅመን ለድል እንድንበቃ በማለም አልነበረም፡፡ ወያኔን ለማስገደድ ወይም ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ላይ የህብረት አስፈላጊነት ባያጠያይቅም ከዚያ በፊት ግን እኛ ራሳችን በቅድሚያ ብቃት ያለው ድርጅት ፈጥረናል ወይ? የሚል ጥያቄ መነሳት ነበረበት፡፡ ቀጥሎ ህብረት ሲባል ምን አይነት አቅምና አላማ ካላቸው ድርጅቶች ጋር ነው ህብረትና ውህደት የምንፈጥረው የሚል ጥያቄ መነሳት መቻል አለበት፡፡ ከዚህ ውጪ “ህብረት ህብረት” ተብሎ ስለተዘመረ እውነተኛ ህብረትና ድል ሊመጣ እንደማይችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡

4. በቱፋ (እንዳርጋቸው ፅጌ) ኤርትራ ውስጥ እየሰለጠነ ነው የሚባለው ሰራዊትም ወሬ ብቻ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በሻዕቢያ የሚሰለጥን አንድም የግንቦት 7 ወታደር የለም፡፡ ቱፋ የድርጅቱን ሃብት ያለ ምንም ውጤት በከንቱ ሲያባክን ከከረመ በኋላ ምን እየሰራህ ነው? ከሚለው የአባላት አስጨናቂ ጥያቄ ለመሸሽ

ሲል ያለ ስራ ኤርትራ ውስጥ ተደብቆ መቀመጥን መርጧል፡፡ ተስፋ መቁረጡና ብስጭቱ ከእድሜ መግፋቱ ጋር ተዳምረው በየሻይቤቱና በየዛፍ ጥላ ስሩ ሲያንጎላጅጅ እንደሚውል እንሰማለን፡፡ ፀረ-ወያኔ የትጥቅ ትግል ለመጀመር ጠንካራና የተማሩ አባላት እያሰባሰብን ነው እያለ ቢያስወራም እስከ አሁን ድረስ ከአውሮፓ የሄደው መሳፍንት አያሌው የሚባል አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡ እሱም ቢሆን እንኳን ሰውን መምራት ቀርቶ ራሱን መቆጣጠርና ቤተሰቡን ማስተዳደር የማይችል በሰለጠነ አለም እየኖረ ሚስቱን ሲደበድብ የሚውል ተራ ሰው መሆኑ ይታወቃል፡፡ በተለያየ አጋጣሚ ደጋግመን እንደተናገርነው አባሉ በቱፋ እየተሰራ ነው ተብሎ የሚነገረው ስራ ሁሉ ውሸት መሆኑን ተረድቶ እስከአሁን ድረስ የነበረው ጉዞ በትክክል እንዲገመገም እውነቱ እንዲወጣ እነዚህን አምባገነኖች ማንቁርታቸውን ይዞ መጠየቅ አለበት፡፡ በዚህ የማጭበርበር መንገድ መቀጠል አትችሉም ማለት መቻል አለበት፡፡ ይህ እስካልተደረገ ድረስ ነገሩ ሁሉ "ላም አለችኝ በሰማይ ወተትዋን የማላይ" ከሚባለው የአገራችን ተረት እንደማያልፍ ልናውቅ ይገባል፡፡

5. ከመለስ ዜናዊ ህልፈት በኋላ በሃገራችን የሚታየው ሁኔታ ከወያኔ ጋር የሚካሄደው ትግል ምን ያህል ከባድና የተወሳሰበ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ተስፋ የሚሰጥ አለመሆኑን ከዚህ ቀደም ገልፀናል፡፡ አስተሳሰበ-ድሃው ካሌብ (አበበ ቦጋለ) ህዝቡ ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ሲገልፅ የከረመውን የሃዘን ስሜት "የኢትዮጵያ ህዝብ ተገዶ ለለቅሶ ሲወጣ እንደነበረ የሚያረጋግጥ ተጨባጭ መረጃ አለን" በማለት አፉን ሞልቶ በአደባባይ ሲናገር ሰምተናል፡፡ የግንቦት 7 አባል እንዲህ አይነት ተራ ወሬ ምንም ያህል ርቀት ሊያስኬደን አይችልም ማለት መቻል አለበት፡፡ የሃገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ ለመለወጥ የሚያስችል በእኛ በኩል ምንም የተሰራ ስራ ሳይኖር መለስ ሞተ አልሞተ የሚያመጣው አንዳችም ለውጥ አይኖርም፡፡ ወደድንም ጠላንም እድሉ አምልጦናል፡፡ አሁን ወያኔ/ኢህአዴግ ከመሪው ህልፈት በኋላ "ራዕዩን" ከማስቀጠል ውጪ በሃገራችን ምንም ዓይነት ለውጥ እንደማይኖር በማያሻማ ቋንቋ እየነገረን ነው፡፡ ግንቦት 7 የራሱ የሆነ ድርጅታዊ አቅም በመገንባት መሬት ላይ ተጨባጭ ስራ መስራት እስካልቻለ ድረስ ከሻዕቢያ ጋር ተጣብቆ ልክ እንደ አነግ በሻዕቢያ ሳንባ እየተነፈሰ እድሜውን በከንቱ ከመቁጠር በቀር ቁም ነገር ሊሰራ እንደማይችል አባሉ ተረድቶ ለለውጥ የጋራ ድምፁን ማሰማት መቻል አለበት እንላለን፡፡

ግንቦት 7 በእነዚህ የውስጥ ውስብስብ ችግሮችና የውጪ ተግዳሮቶች ተተብትቦ የዛሬ አራት አመት ሲመሰረት ከነበረው ድርጅታዊ ይዞታ ዛሬ ፍፁም የተዳከመበት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አምባገነን መሪዎቻችን መራራ እውነቱን በውሸት ለመሸፋፈን በከንቱ ቢደክሙም መላው የግንቦት 7 አባል ግን ሃቁን አሳምሮ ያውቀዋል፡፡ እነዚህ ውስብስብ ችግሮች ደግሞ ድርጅቱ ለመውደቅ በገደል አፋፍ ላይ መሆኑን እንጂ አስካዱ (ብርሃኑ ነጋ)፣ ካሌብ (አበበ ቦጋለ)፣ ታደሰ ብሩ (ሚያዝያ) እና ሌሎች የግንቦት 7 መሪዎች ለማጭበርበር እንደሚሞክሩት ለድል እየተቃረበ መሆኑን በፍፁም የሚያመለክቱ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ላለፉት አራት አመታት በአጓጉል የድል ተስፋ ጊዜውን፣ ገንዘቡንና፣ ጉልበቱን ሲገብር የነበረው መላው የግንቦት 7 አባል ጊዜው ሳይመሽ እነዚህን አምባገነኖች ከአሁን በኋላስ በቃችሁ፣ አትዋሹን ድርጅቱን የመምራት ብቃት ስለሌላችሁ ሃላፊነታችሁን በአስቸኳይ ልቀቁ ሊላቸው ይገባል፡፡

ድል ለኢትየጵያ ህዝብ!!
የግንቦት 7 የእርምት ንቅናቄ ቡድን፡፡